## רפורמת הלמידה המשמעותית – פרסום שאלון לדוגמא (30%)

מבחן של השפה האמהרית

מנהל תחום דעת: ד"ר אנבסה טפרה

ג' טבת תשע"ו 15 דצמבר 2015

| | |
|---|---|
| አስተውል! መልሶችህን በግልጽና በትልልቅ ፊደሎች በእስክሪብቶ ብቻ ጻፍ | שים לב: את התשובות כתוב ברור, בעט (ולא בעיפרון) ובאותיות גדולות |

| | |
|---|---|
| **ክፍል አንድ** (70 ነጥብ)<br>ከታች በክፍል የተማርከው ምንባብ አለ። የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። | **<u>פרק ראשון</u>** (70 נקודות) **<u>קטע שנלמד</u>**<br>קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 1-10 בעברית או באמהרית. |

# <u>አንበሳና አይጥ</u>

አንድ አንበሳ በጣም ራበውና በሰፊ የሣር ሜዳ (savannah) ላይ ሲ ር ሚዳቋ አገኘ። ሚዳቋንም ገድሎ በላና ሲጠግብ ወደ ጉሬው ሄዶ ተኛ። በዚህም ጊዜ እንቅልፍ ወሰደው። አንዲት አይጥ በአንበሳው ጉሬ ስትዘዋወር አንበሳውን ነካችና አንበሳው ከእንቅልፉ ነቃ። “ለምን ከባድ እንቅልፍ ላይ ያለሁትን ቀሰቀስሽኝ?” ብሎ አይጥዋን በጣም ተቆጣት። ከመሬት ብድግ አደረጋትና ዓ ይኑን አፈጠጠባት። አይጥዋም በጣም ፈራችና ዓይንዋን ቁልጭ ቁልጭ ታደርግ ጀመር።

በኋላም እያለቀሰች “እባክዎን አይግደሉኝ አንድ ቀን እረዳዎታለሁ” አለችው። “አንቺ ደግሞ ምን ትረጅኛለሽ?” አለና አንበሳው በጣም ተቆጣ። አይጥዋም “እባክዎን ጌታዬ ይማሩኝ” አለችው። አንበሳውም አሳዘነችውና ለቀቃት።

አንድ ቀን አንበሳው በአዳኞች ወጥመድ ተያዘ። ከወጥመዱም ማምለጥ ስላልቻለ ይጮኽ ነበር። በዚህ ጊዜ ያቺ አይጥ ጩኸቱን ሰማችና ወደ አንበሳው ሄዳ “ጌታዬ ምን ሆኑ?” አለችው። እሱም “በወጥመድ ተይዤለሁ” አላት። አይጥዋም አንበሳው ሳይገድላት የለቀቃትን ቀን አስታወሰች። ከዚያም “አይ ዎት አይፍሩ እኔ እረዳዎታለሁ” አለችና ወጥመዱን በመጋዝ ጥርሷ መቁረጥ ጀመረች። ወጥመዱን ብዙ ቦታ በጣጠሰችውና አንበሳው ከወጥመዱ ወጣ። አንበሳውም ከወጥመዱ በመውጣቱ በጣም ተደስቶ ደስ ብሎ አመሰገናት። አይጥዋም “ምንም እኛ አይጦች ትንንሽ ፍጥረቶች ብንሆንም ውለታ መመለስ እንወዳለን” አለችው።

| **ጥያቄዎች** (70 ነጥብ) በምንባቡ መሠረት ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 7 ነጥብ አለው። በጠቅላላ 70 ነጥብ።) | **<u>השאלות</u>** (70 נקודות) **<u>קטע שנלמד</u>** ענה על השאלות 1-10 בעברית או באמהרית לפי הקטע. (לכל תשובה נכונה – 7 נקודות; סה"כ –70 נקודות) |
|---|---|

1. አንበሳው ሚዳቋዋን ያገኘው የት ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2. አንበሳው ሚዳቋዋን ከበላ በኋላ ምን አደረገ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3. አንበሳው ከእንቅልፍ የነቃው ለምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. ከእንቅልፍ ከነቃ በኋላ አንበሳው አይጥዋን ምን አላት?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

5. አይጥዋ ዓይንዋን ቁልጭ ቁልጭ ያደረገችው ለምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

6. አይጥዋ እያለቀሰች ለአንበሳው ምን አለችው?

___

___

7. አንድ ቀን አንበሳው ይጮኽ የነበረው ለምንድን ነው?

___

___

8. አንበሳው በወጥመድ መያዙን ሲነግራት አይጥዋ ምን አለችው?

___

___

9. አንበሳው ከወጥመዱ የወጣው እንዴት ነው?

___

___

10. አንበሳው ሲያመሰግናት ጊዜ አይጥዋ ምን አለችው?

___

___

| | |
|---|---|
| **ክፍል ሁለት** - የሰዋስው ጥያቄዎች<br>(20 ነጥብ)<br>ከ11-18 ላሉት ጥያቄዎች 4 ምርጫዎች ተሰጥተዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ክበብ። (እያንዳንዱ ጥያቄ 2.5 ነጥብ አለው፣ በአጠቃላይ 20 ነጥብ።) | <u>פרק שני</u> (20 נקודות) <u>שאלות לשון</u><br>ענה על כל השאלות 11-18. בכל שאלה הקף במעגל את האות מסמנת את האפשרות הנכונה, מבין 4 אפשרויות הנתונות.<br>(לכל תשובה נכונה – 2.5 נקודות;<br>סה"כ – 20 נקודות) |

11. ሰማ ብሎ አዳመጠ ካለ አየ ብሎ ___ ይላል።

ሀ. አላየም ሐ. አመለከተ

ለ. ተመለከተ መ. ለ እና ሐ

12. ልበ-ቢስ ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ ማን ነው?

ሀ. ስስታም ሐ. ልብ አውልቅ

ለ. የማያስተውል መ. ደፋር

13. መጣ ብሎ ሄደ ካለ ራቀ ብሎ____ ይላል።

ሀ. ሸሸ ሐ. ሩቅ ሆነ

ለ. ቀረበ መ. አልራቀም

14 ማሰነ ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ ማን ነው

ሀ. ደከመ ሐ. ጉድጓድ ቆፈረ

ለ. በረታ መ. ለ እና ሐ

15. ሰጠ ብሎ____ ካለ ሄደ ብሎ አካሄድ ይላል።

ሀ. ስጦታ ለ. ሰጪ

ለ. አሰጣጥ መ. አቀባበል

16. ከእነዚህ ቃላት መካከል ሁለት አጠራርና ሁለት ትርጉም ያለው የትኛው ነው

ሀ. ጋራ ሐ. ቤት

ለ. አለ መ. ጣራ

17. ሰውዬው "እጁ አጠረ" ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ሀብታም ሆነ          ሐ. ተደሰተ

ለ. ተቸገረ          መ. ሥራ ፈታ

18. ሴትዮዋ "አራስ ነብር ነች" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አውሬ          ሐ. ረጅም ጥፍር የላት

ለ. በቅርቡ የወለደች          መ. ቶሎ የምትቆጣ

| | |
|---|---|
| **ክፍል ሦስት** - ምሳሌያዊ አነጋገሮች<br>(10 ነጥብ)<br>ከ19-23 ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟላ።<br>(እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ 2 ነጥብ አለው፥ በጠቅላላ 10 ነጥብ) | **פרק שלישי - פתגמים**<br>(10 נקודות)<br>השלם חמש פתגמים מ19 עד 23. (לכל השלמה נכונה – שתי נקודות; סה"כ – 10 נקודות) |

19. ______________________ ፣ ከምግብ መለየት።

20. ____________________________ ፣ ከመዳብ ይቆጠራል።

21. ሳለፈ ክረምት ፣ ________________________።

22. ጅብን ፈርቼ ዛፍ ላይ ብወጣ፣ ________________________________።

23. ________________________________ ፣ አንበሳ ያስር።